# ትምህርት 65

1. ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው፥ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት እርሱን እንድናገለግል ፈልጎ ነው?

ሀ- አይደለም።

2. ኢየሱስ ምን ላደርግ ወደዚህ ዓለም መጣሁ አለ?

ሀ- ሰዎችን ለማገልገልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት።

3. የበርጠሜዎስ ዓይነ ስውርነት ስለ ሰዎች ምን ያሳስበናል?

ሀ- በርጤሜዎስ ዓይነ ስውር እንደ ሆነ ሁሉ ሰዎች እውር ሆነው መወለዳቸውን።

4. ሰዎች ዓይነ ስውር ሆነው የተወለዱት እንዴት ነው?

ሀ- ሰዎች ሁሉ ከአዳምና ሄዋን ስለተወለዱ ለእግዚአብሔር እውነቶች ዓየነ ስውራን ሆነዋል።

5. በርጤሜዎስ እንደገና ማየት እንዲችል፥ በራሱ ማድረግ የሚችለው ነገር ነበር?

ሀ- አልነበረም።

6. ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነቶች ለማየት እንዲችሉ በራሳቸው ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች አሉ?

ሀ- የሉም።

7. የበርጤሜዎስ ዓይን እንዲያይ የማድረግ ችሎታ ያለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ።

8. የሰዎችን ዓይን ማብራት የሚችለው ማን ብቻ ነው?
ሀ- ኢየሱስ።

9. በርጤሜዎስ ኢየሱስን የዳዊት ልጅ ብሎ የጠራው ለምንድን ነው?
ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ፥ አዳኝ ይሆናል ብሎ እግዚአብሔር ተስፋ የገባው የንጉስ ዳዊት ዘር ስለ ነበር።

10. ሰዎች በርጤሜዎስ ጸጥ እንዲል የገሰፁት ለምን ነበር?
ሀ- ሰዎች ኢየሱስ ደሃውን ዓይነ ስውር ለማኝ የሚረዳ ስላልመሰላቸው።

11. ኢየሱስ ደሃውን ዓይነ ስውር ለማኝ ለመርዳት ፈለጓል?
ሀ- አዎን።

12. እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በመውደድ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ይፈልጋል?
ሀ- አዎን።

13. ኢየሱስ፥ በርጤሜዎስ ማየት እንዲችል ማድረግ ችሎ ነበር?
ሀ- አዎን።

14. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሕዝቡን ከሮማውያን አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ነበር?
ሀ- አይደለም።

15. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ለምን ነበር?
ሀ- ኢየሱስ የሄደው ሕዝቡን ከኃጢአት፥ ከሞትና ከሰይጣን ነፃ ለማውጣት ነበር።

- የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ስለ ጠሉት እርሱን ለመግደል ይፈልጉ ነበር።

ማርቆስ 14፡1-2

1- ፋሲካና የቂጣ በዓል ሊከበር ሁለት ቀን ሲቀረው፥ የካህናት አለቆችና ጸሐፍት ኢየሱስን የሚይዙበትና የሚገድሉበትን ዘዴ ይፈልጉ ነበር።

2- ሆኖም «ሕዝቡ ዐመፅ እንዳያስነሣ በበአሉ ሰሞን መሆን የለበትም» ይባባሉ ነበር።

- የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን በፋሲካ በዓል ለመያዝ ያልፈለጉት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስን በፋሲካ በዓል ሰሞን ከያዙት ሕዝቡ ዐመፅ ያስነሳል የሚል ፍርሃት ስለነበራቸው ነው።

ማርቆስ 14፡10

10- ከዚህ በኋላ ከዐስራ ሁለቱ አንዱ የሆነው የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ የሰጠው ወደ ካህናት አለቆች ሄደ።

- ይሁዳ ማን ነበር?

- ይሁዳ ኢየሱስ ከመረጣቸው አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር።

- ይሁዳ በኃጢአት መወለዱንና የኢየሱስ አዳኝነት የሚያስፈልገው መሆኑን ያውቅ ነበር?

- አያወቅም።

- ይሁዳ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አምኗል?

- አላመነም።

- ይሁዳ ኢየሱስን የተከተለው አዳኝ አምላክ መሆኑን ስላመነ አይደለም።

- ታዲያ ይሁዳ ኢየሱስን ለምን ተከተለው?

- ይሁዳ ኢየሱስን የተከትለው ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ነበር።

- ይሁዳ ከኢየሱስ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ባለመቻሉ ኢየሱስን ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ የመራው ማን ነበር?
- ሰይጣን።

- ሰይጣን ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ የፈለገው ለምን ነበር?

- ኢየሱስን ስለሚጠላ።

- ሰይጣን ኢየሱስን የሚጠላው ለምንድነው?

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ።
- ኢየሱስ እውነትን ስለሚናገር።

- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉ ፈለገ።

- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉ የፈለገው ለምንድነው?

- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት የፈለገው፥ ኢየሱስ እኛን እንዳያድነን ስለፈለገ ነው።

- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት የፈለገው፥ ኢየሱስ የኃጢአትንና የሞትን ኃይል እንዳያጠፋ ነው።

- ሰይጣን የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንዲገድሉ የፈለገው፥ ኢየሱስ የራሱ የሰይጣንን ሀይል እንዳያጠፋ ነው።

- ስለዚህ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ወደ አይሁድ መሪዎች ሄደ።

- ነቢያት አዳኙን ማን አሳልፎ እንደሚሰጥ ተናገሩ?
- የቅርብ ወዳጁ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል እንደተናገረው፥ የቅርብ ወዳጁ ኢየሱስን አሳልፎ ሰጠ።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመሰጠት ወደ አይሁድ መሪዎች ሲመጣ የአይሁድ መሪዎች ምን አሰቡ?

ማርቆስ 14፡11

11- የካህናት አለቆች ይህን ሲሰሙ ደስ አላቸው፤ ገንዘብ ሊሰጡትም ቃል ገቡለት፤ ስለዚህ እርሱን አሳልፎ የሚሰጥበትን ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር።

- የካህናት አለቆች ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጣቸው ሠላሳ ብር ለመስጠት

ቃል ገቡ።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው በምን ያህል ገንዘብ ነበር?

- በሰላሳ ብር።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት በተናገረው መሰረት ኢየሱስ በሰላሳ ብር ተሸጠ።

- በቂጣ በዓል የመጀመሪያ ቀን፥ ደቀመዛሙርት ኢየሱስን ምን ጠየቁት?

ማርቆስ 14፡12

12-የፋሲካ በግ በሚታረድበት በቂጣ በዓል የመጀመሪያ ቀን ደቀመዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፥ «የፋሲካ እራት የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?» አሉት።

- ደቀመዛሙርቱ የፋሲካን በዓል እራት የት እናዘጋጅ ብለው ኢየሱስን ጠየቁት?

- የፋሲካ በዓል ምን ነበር?

- የፋሲካ በዓል አይሁድ በግብፅ የተፈፀመውን የሚያስታውሱበት በዓል ነበር።

- በግብፅ  ምን ተፈፀመ?

- እስራኤላውያን በግ ስላረዱና የበሮቻቸውን  መቃኖች በደሙ ስለቀቡ እግዚአብሔር የበኵር ልጆቻቸውን ሳይገድል አለፈ።

-ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል መለሰ፦

ማርቆስ 14፡13-15

13- እርሱም ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ ሲል ላካቸው!«ወደ ከተማ ሂዱ እንስራ ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤

14- ወደ ሚገባበት ቤትም ተከተሉት፤ የቤቱንም ጌታ፥ «መምህሩ፥ ከደቀመዛሙርቴ ጋር የፋሲካን እራት የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ የትኛው ነው” ብሎአል በሉት።

15- እርሱም በሰገነቱ ላይ የተሰናዳና የተነጠፈ ሰፊ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያ አዘጋጁልን»።

- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በእንስራ ውሃ የተሸከመውን ሰው እንደሚያገኙና ተከትለውት በመሄድ ወደሚገባበት ቤት እንዲገቡ ነገራቸው።

- ውኃ በእንስራ የሚሸከሙት ሴቶች ብቻ መሆናቸው ቢታወቅም፥ በዚህን ጊዜ በእንስራ ውኃ የሚሸከመው ወንድ እንድሚሆን ኢየሱስ አውቋል።

- ኢየሱስ ስለ ሰው ሁሉ፥ ሁሉንም ነገር ያውቃል ።

- ኢየሱስ የማያውቀው ነገር የለም።

- ደቀመዛሙርቱ የፋሲካን የበዓል እራት የሚያዘጋጁት ሰውየው በገባበት ቤት ውስጥ ነበር።

- ደቀመዛሙርቱ በእንስራ ውኃ የተሸከመውን ሰው አግኝተዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ማርቆስ 14፡16

16- ደቀመዛሙርቱ ወጥተው ወደ ከተማዪቱ ሄዱ፤ ማንኛውንም ነገር ኢየሱስ እንዳለው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካውንም አሰናዱ።

- ደቀመዛምሙርቱ ለፋሲካው በዓል ካሰናዱ በኋላ ሲመሽ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ወደዚያ ቤት ገቡ።

ማርቆስ 14፡17-18

17- በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከአስራ ሁለቱ ጋር መጣ።

18- በማዕድ ላይ ሳሉም፥ «እውነት እላችኋለሁ፥ ከመካከላችሁ አንዱ፥ አብሮኝ የሚበላው እርሱ አሳልፎ ይሰጠኛል» አላቸው።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ አብረው በመብላት ላይ ሳሉ ኢየሱስ ምን አላቸው?

- ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ተናገረ።

- ኢየሱስ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቃል።

- ኢየሱስ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው እንዴት አወቀ?

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ያውቃል።

- ኢየሱስ የማያውቀው ምንም ነገር የለም።

- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ከእነርሱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ለምን ተናገረ?

- ኢየሱስ ይሁዳ ሊያደርግ ስላለው ነገር እንዲያስብ ፈልጎ ነበር።

- ኢየሱስ ይሁዳ ንሰሐ እንዲገባ ፈለጎ ነው።

-ኢየሱስ ይሁዳ አሳቡን እንዲለውጥ፥ የተቀበለውን ገንዘብ እንዲመልስና እርሱን አሳልፎ እንዳይሰጥ ፈለገ።

- ከዚያም ደቀመዛሙርቱ ምን አሉ?

ማርቆስ 14፡19-20

19- ደቀመዛሙርቱም አዘኑ እያንዳንዳቸውም «እኔ እሆንን?» ይሉት ጀመር።

20- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ከአስራ ሁለቱ አንዱ፥ ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ውስጥ የሚያጠልቀው ነው።»

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ አብረው በመመገብ ላይ ስለነበሩ፤ ኢየሱስ እርሱን አሳልፎ የሚሰጠው እጁን በወጭቱ ውስጥ ከእርሱ ጋር የሚከተው ሰው እንደሆነ ተናገረ።

- አይሁዶች አብረው በሚበሉበት ጊዜ ዳቦውን ይቆርሱና ማእዱ መሃል፥ በወጭቱ ውስጥ ካለው ወጥ ውስጥ ያጠቅሳሉ።

- ኢየሱስ እርሱን የሚክደው ከእርሱ ጋር አብሮ የሚበላ ሰው መሆኑን ተናገረ።

- በድጋሚ ኢየሱስ ይሁዳ ሊያደርግ ስላለው ነገር እንዲያስብ ፈለገ።

- ከሰው ጋር አብሮ መብላትና ያን ሰው አሳልፎ መስጠት ክፉ ነገር ነው?

-አዎን በጣም ክፉ ነገር ነው።

- ቀጥሎስ ኢየሱስ ምን አለ?

ማርቆስ 14፡21

21-ኢየሱስ እንዲህ አለ «የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ የሰውን ልጅ አሳልፎ ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ግን ወዮለት፤ ያ ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር።»

- ኢየሱስ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ የጠራው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ፍፁም ሰው ስለ ነበር ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ የመጣው እንደ ልጅ ሰዎችን ለማገልገል ስለ ሆነ ነው።

- ኢየሱስ እንደሚሞት ያውቃል።

- ኢየሱስ ቢሞትም፥ ኢየሱስን አሳልፎ በሚሰጠው ሰው ላይ ከፍ ያለ ቅጣት ይደርስበታል።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ እግዚአብሔር አላስገደደውም።

- ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ በመስጠቱ የዘላለም ቅጣት ይቀጣል።

- እራት በመብላት ላይ ሳሉ ኢየሱስ በድጋሚ ለደቀመዛሙርቱ ተናገረ።

ማርቆስ 14፥22

22- ሲበሉም እንጀራ አንስቶ ባረከ፤ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸውና፥ «እንኩ፤ ይህ ስጋዬ ነው» አላቸው።

- ኢየሱስ እንጀራ አንስቶ እግዚአብሔር አብን ካመሰገነ በኋላ እንጀራውን ቆርሶ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው።

- ኢየሱስ እንጀራው የእርሱ ስጋ ምሳሌ መሆኑን ተናገረ።

- እንጀራው የኢየሱስ ሥጋ ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው?

- እንጀራው እንደ ተቆረሰ ሁሉ የኢየሱስም ሥጋ በክፉ ሰዎች እጅ የሚቆረስ መሆኑ።

ማርቆስ 14፥23-24

23- ኢየሱስ ፅዋውንም አነሣ፤ አመስግኖም ሰጣቸው፤ ሁሉም ከዚያ ጠጡ።

24-ደግሞም እንዲህ አላቸው «ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው። ”

- ከዚያ ኢየሱስ የወይኑ ፅዋ አንስቶ እግዚአብሔርን ካመሰገነ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው።

- ኢየሱስ ወይኑ የደሙ ምሳሌ መሆኑን ነገራቸው?

- ወይኑ የኢየሱስ ደም ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው?

- ወይን ለመጠጣት እንደሚቀዳ ሁሉ የኢየሱስ ደምም የሚፈስ በመሆኑ።

- ኢየሱስ ደሙ የሚፈሰው ለማን ነው አለ?

- ኢየሱስ ደሙ ሚፈስሰው ለብዙ ሰዎች ነው አለ።

- በልተው እንደጨረሱ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ አንደገና ተናገራቸው።

ማርቆስ 14፡25-26

25- ኢየሱስ እንዲህ አለ «እውነት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግስት አዲሱን የወይን ፍሬ እስከምጠጣበት እስከዚያች ቀን ድረስ ዳግም ይህን አልጠጣም።»

26-ከዚህ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ ደብረ 9ዘይት ተራራ ወጡ።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በልተው እንዳበቁ መሽቶ ነበር።

- በልተው ካበቁ በኋላ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ኢየሩሳሌምን ለቅቀው ወደ ደብረዘይት ተራራ ወጡ።